# ቅጣው አባደፋር!

ከኪነጥበብ (ለንደን) ጥር 1998 ዓ.ም.



ቅጣው አባደፋር! ልበሙሉው ወጣት፣
የይሕዋው ቀዛፊ፣ ማእምረ ፈለካት፣
ኢትዮጵያዊው ጀግና፣ የናሳው ሳይንቲስት፣
መርዶህን የሰማ፣ ኢትዮጵያዊ ሁሉ፣
እንደእንጨት ደረቀ፣ አዘነ በሙሉ።

ኢትዮጵያ እናታችን፣ ችግሯ ብዙ ነው፣
ይኸን ላንተ መንገር፣ ለሰሚው ማርዳት ነው።
የእናት አገርህን፣ የደለበ መሬት፣
ገና ያልተጠናው፣ የአየሩ ንብረት፣
የኢትዮጵያ ሰማይ፣ የኢትዮጵያ ምድር፣
የናሳ ሳይንቲስት፣ አይፈልግም ነበር?
ለሰሚው ግራ ነው፣ ቅጣው ያንተ ነገር።
ያገርህን ሰማይ፣ ያገርህን መሬት፣
እንደዚያ ስትናፍቅ፣ ስታልም ቀን ከሌት፣
ወደሌላው ዓለም፣ ምነው ዘመትክ ድንገት?!

ቅጣው ያንተን ውጤት፣ ኢትዮጵያ ሰምታ፣
ደስታዋን ሳትገልጽ፣ ምኞቷን አሟልታ፣
እንዴት እንደዋዛ፣ እንደዚህ ትረታ?!

ተምረህ ተምረህ፣ የሊቅ ሊቅ ሆነህ፣
የእናትህን አዘን፣ ብሶቷን ሰምተህ፣
ሰላም እንደሌላት፣ ግፏን ተረድተህ፣
ለማውጣት ወስነህ፣ እሾሁን በእሾህ፣
ቅጣው! ቅጣው! ስንል፣ ጠፋብን ድምጽህ።

በአርበኞች ግንባር፣ ጦር አሰልፈህ፣
ምነው ድምጽህ ጠፋ?! ሁሉም ሲጠራህ?!
ቅጣው! ቅጣው! እያልን ገና ስንፎክር፣
እንደምን ተሸነፍክ፣ በውጥን በጅምር?!

በዓላማህ አምኖ፣ ብዙ ተሰልፏል፣
ሰላም ካሳሰረ?! ምን ምርጫ ይኖራል?!
ሰላም ካስገደለ?! ምን ምርጫ ይኖራል?!
ወያኔ ካልገባው፣ ሰላማዊ ትግል፣
ከውጊያ በስተቀር፣ ምን ምርጫ ይኖራል?!
የሚለው አቋምህ፣ በጣም ተደግፎ፣
ቅጣው! ቅጣው! ብሏል ሁሉም አሰፍስፎ፤
እባክህ ቀና በል፣ ቅጣው የእኛ ጀግና፣
ጠላት በያለበት፣ ተደናግጧል እና።

ፕሮፌሰር አስራት፣ ወዳጅ ከፈለጉ፣
የናሳው ሳይንቲስት፣ ባለማዕረጉ፣
ያው መጥቶሎታል፣ ልጅ ቅጣው እጅጉ፣
የኢትዮጵያን ጉዳይ፣ በሚገባ ያውጉ፣
ትግሉ ተቀጣጥሏል፣ እጅግም አይስጉ፤
በጣም ይጠይቁት፣ ያጫውተዎታል፣
ስለሰማዩም ቤት፣ ብዙ ነገር ያውቃል።

አየ ጉድ! እናንተ፤ ከንቱ ነው ሰው መሆን፣
ያ ቅጣው እጅጉም፣ ሞቷል ሲባል ሰማን።

የቅጣው ቤተሰብ፣ እግዚአብሔር ያጥናችሁ፣
የግንባር አርበኞች፣ እግዚአብሔር ያጥናችሁ፣
እሱም ሰው ነውና፣ ይጠንክር ልባችሁ፤
መቼስ ምን ምርጫ አለን?! ምን ምርጫስ አላችሁ?!
መከተል ብቻ ነው፣ አርማውን ይዛችሁ!